IFLA

# የቤተ-መጻሕፍትን ድርጅታዊ አወቃቀር ለማበጀት እንዲያግዝ የተዘጋጀ መምሪያ

**መግቢያ**

ማህበራት የሚደራጁት አባሎቻቸውን እንዲያገለግሉ ነው። ሰዎች በቀላሉ እንዲረዱት ሆኖ የተዘጋጀ የአንድ ማህበር ድርጅታዊ አወቃቀር ለማህበሩ ሥራ ውጤታማነትና ብቃት እጅግ ወሳኝ ነገር ነው። አደረጃጀቱ ማህበሩ የሚገኝበትን ሀገር ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊ እና የዕድገት ደረጃ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ ማስገባት የሚኖርበት ሲሆን ከእነዚህ ሁኔታዎችም በመነሳት የተለያየ መልክ ሊኖረው ይችላል። አደረጃጀቱ በማህበሩ የተለያዩ ክፍሎች ማለትም በቦርድ፣ በኮሚቴዎች፣ እና ውሱን ለሆኑ ጉዳዮች በሚደራጁ ግብረ-ሃይሎች መካከል እና በአጠቃላይ በአባላትም መካከል ሊኖር ስለሚገባው ግንኙነት ይወስናል። እንዲሁም አደረጃጀቱ ማህበሩን ለአባላቱ ቅርብ በማድረግ ረገድ ሊረዳ ይችላል።

ይህ በራሪ ወረቀት ዓለምአቀፍ የቤተ-መጻህፍት ማህበራትና ድርጅቶች ፌዴሬሽን ያወጣቸውን በራሪ ወረቀቶች ማለትም የቤተ-መጻህፍት ማህበራትን ስለመምራትና ማስተዳደር ያወጣውን መምሪያ፣ ስለቤተ-መጻህፍት ማህበራት የሥራ አመራር ያወጣውን መምሪያና እንዲሁም ስለቤተ-መጻህፍት ማህበራት ፖሊሲዎችና የአሰራር ሥርዓት ያወጣውን መምሪያ የሚደግፍ ነው።

**የድርጅታዊ አወቃቀር ክፍሎች**

የማህበሩ ህገ-ደንቦች ለማህበሩ ድርጅታዊ አወቃቀር ማለትም የማህበሩን የአባልነት ደረጃዎች፣ የአመራር አካላት፣ ቋሚ ኮሚቴዎች፣ ዋና ዋና ተመራጭና ተሿሚ የሥራ ሃላፊዎችን እና ሌሎች የማህበሩን የሥራ ክፍሎች በመወሰንና እንዲሁም የሥራ ድርሻዎችን፣ ሃላፊነቶችንና እያንዳንዳቸው ሊያሟሏቸው የሚገቡ የብቃት መስፈርትን በማስቀመጥ ለማህበሩ የህግ መሰረት ይጥላሉ።

የአንድ ማህበር መሠረታዊ ዓላማዎች በማህበራት ምስረታና ምዝገባ የሕግ ሰነድ ውስጥ በዝርዝር ተመልክተው ይገኛሉ። ይህ ሰነድ በአንዳንድ ቦታዎች የመመሥረቻ ጽሁፍ ወይም ቻርተር የሚል ስያሜ አለው። በዚህ ሰነድ ውስጥ የሚመለከቱት ዓላማዎች በማህበሩ አወቃቀር ውስጥ በግልጽ መታየት ይኖርባቸዋል። ለምሳሌ ማህበሩ ለአባላቱ ተከታታይ ሙያዊ ሥልጠና መስጠት አንድ የተቀመጠ ዓላማው ከሆነ ይህንን ተግባር ሥራ ላይ የሚያውል ቡድን በማህበሩ አወቃቀር ውስጥ መመልከት ይኖርበታል።

በማህበሩ ውስጥ ጎን ለጎን የሚራመዱ የተለያዩ የድርጅታዊ አወቃቀር ክፍሎች ይኖራሉ። በእነዚህ ልዩ ልዩ ክፍሎች ውስጥ የሚኖሩት ቡድኖች እንደመጠናቸው፣ እንደየዝንባሌያቸው ልዩነት፣ እንደተልዕኮ ወሰናቸው እና እንደማህበሩ ሌሎች የሥራ ባህርያት የተለያዩ ሊሆኑ ይችላሉ።

**አመራር**

አንድ ማህበር በፖሊሲ ማውጣት፣ በፋይናንስ እና በሌሎች ጉዳዮች የመጨረሻውን ውሳኔ ሊሰጥ የሚችል የዲሬክተሮች ቦርድ ወይም ካውንስል ኖሮት ሌሎች የሥራ ሃላፊነት ያላቸው እርከኖች ይኖሩታል። በቦርዱ ወይም በሥራ አስፈጻሚው የሥራ መሪነት ሥር ኮሚቴዎች፣ ለአንድ ውሱን ለሆነ ተግባር የሚደራጁ ግብረ-ሃይሎች፣ የሌሎች ድርጅቶች ተወካዮች፣ በክፍያ የሚሰራ ሃላፊ እና ሌሎች የሥራ ክፍሎች ሊኖሩት ይችላሉ። የሥራ መሪዎችና ቡድኖች ቁጥር፣ ተግባር እና ሃላፊነቶች እንደማህበሩ መጠንና ተልዕኮ ሊለያይ ይችላል። በዚህ በራሪ ወረቀት መጨረሻ ላይ የአንድ ማህበር ድርጅታዊ አወቃቀር መግለጫ ምን ሊመስል እንደሚችል እንደምሳሌ ተመልክቷል። መግለጫው የማህበሩን ከፍተኛ ውሳኔ-ሰጭ አካል ከላይ በማድረግ የማህበሩን ዕርከናዊ አደረጃጀት ያሳያል። የማህበሩን ድርጅታዊ አወቃቀር በግልጽ መረዳት ከተቻለ አባላት የሚኖሯቸው ጉዳዮች እንዲታዩላቸውና እርምጃ እንዲወሰድባቸው ለማድረግ ይረዳቸዋል። የሥራ ሃላፊዎች፣ ተሿሚ ባለሥልጣናት እና ዋና የሥራ መሪው ያላቸውን የሥራ ድርሻ የሚያመለክት የሥራ መዘርዝር ማዘጋጀት የሥራ ድርሻና ሃላፊነቶች መደራረብ እንዳይኖር ያግዛል።

ኮሚቴዎች፣ ለአንድ ውሱን ለሆነ ተግባር የሚደራጁ ግብረ-ሃይሎች እና ሌሎች ተመሳሳይ የሥራ ክፍሎች የየቡድናቸውን ዓላማ፣ ሥራ ላይ የሚቆዩበትን የተወሰነ የሥራ ዘመን፣ ሊኖሯቸው የሚችሉትን የአባላት ብዛት፣ ከሌሎች የማህበሩ ክፍሎች አብዛኛውን ጊዜ ከዲሬክተሮች ቦርድ ወይም ከፍተኛ አመራር አካል ጋር ያሉ የሪፖርት አቀራረብ ግንኙነቶችን የሚያመለክቱ መምሪያ መግለጫ ሊኖራቸው ይገባል። ክፍሎች ወይም ሌሎች ሙያዊ የዝንባሌ ቡድኖች ተጠሪነታቸው በቀጥታ ለማህበሩ ከፍተኛ አመራር ሆኖ የራሳቸው መተዳደሪያ ህግ ሊኖራቸው ይችላል። ይህ መተዳደሪያ ህግ ከዋናው የእናት ማህበር መተዳደሪያ ህግ ጋር ተቃርኖ እንዳይኖረው ማረጋገጥ ያስፈልጋል።

### ስትራቴጂክ እና የሥራ ዕቅዶች

ድርጅታዊ አወቃቀሩ የስትራቴጂክ ዕቅዱን ዓላማዎች መደገፍ ይገባዋል። ለምሳሌ የማህበሩ አንዱ ዓላማ የማህበሩን አባላት ቁጥር ማሳደግ ከሆነ በማህበሩ አወቃቀር ውስጥ ይህን ዓላማ ለማሳካት የሚሰራ ኮሚቴ ወይም ሌላ ቡድን እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ በድርጅታዊ መዋቅሩ ውስጥ ያሉ ነገር ግን የማህበሩን ግቦችና ዓላማዎች መደገፋቸው ያበቃ ክፍሎች ካሉ እነዚህ ክፍሎች ከመዋቅሩ ውስጥ ስለሚሰረዙበት ሁኔታ እንደገና ማሰብ ያስፈልጋል።

የስትራቴጂክ ዕቅዱ ከማህበሩ የሥራ ዕቅድና በጀት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደመሆኑ ድርጅታዊ መዋቅሩም የሥራ ዕቅዱን ሊደግፍና የሥራ ዕቅዱም ድርጅታዊ መዋቅሩን ሊደግፈው ይገባል። ለምሳሌ ኮሚቴዎች እንዲፈፅሙ የተቋቋሙለትን ግብ ለመምታት እንዲችሉ በቂ በጀት ሊመደብላቸው የሚገባ ሲሆን በሥራ ላይ ላሉ ቡድኖችም በቂ በጀት የተመደበለት የሚፈፅሙት የሥራ ድርሻ ስለመኖሩ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

### በአካባቢ ስለሚደራጁ ቡድኖች

ብሄራዊ ማህበሩ አንዳንድ ጊዜ ከግለሰብ አባላቱ እጅጉን የራቀ መስሎ ሊታይ ይችላል፡፡ ስለዚህም ማህበሩን ለግለሰብ አባላቱ ቅርብ ለማድረግ አካባቢያዊ ወይም ክልላዊ ቡድኖችን ከማህበሩ አወቃቀር ጋር አንድ አካል በማድረግ ማደራጀት ይቻላል፡፡ ማህበሩ በዚህ መልኩ ከተደራጀ  አባላቱ በማህበሩ ወጪ በሚሸፈኑ ዝግጅቶች ላይ ለመገኘት እንዲችሉና በማህበሩ አጠቃላይ እንቅስቃሴዎች ውስጥ መሳተፍ እንዲችሉ ማመቻቸት ያስችለዋል፡፡ እነዚህ ቡድኖች የማህበሩ አንድ ህጋዊ አካል ሊሆኑ ወይም ራሳቸውን ችለው የተቋቋሙ ነገር ግን በማህበሩ ፖሊሲና ህገ-ደንብ መሰረት ከማህበሩ ጋር በቅርበት የሚሰሩ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

### ከሙያ ዝንባሌ አንፃር የሚደራጁ ቡድኖች

በማህበሩ ውስጥ በተለይም ማህበሩ በአቅሙና አደረጃጀቱ ትልቅ ማህበር ከሆነ በውስጡ ሙያዊ ዝንባሌ፣ ችሎታና የሥራ አፈፃፀም ያላቸው ወይም ተመሳሳይ በሆኑ ቤተ-መፃህፍት ውስጥ የሚሰሩ ባለሙያዎች በማህበሩ መዋቅር ውስጥ ራሱን የቻለ ክፍል ወይም ቡድን እንዲኖራቸው መደገፍ ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ የቴክኒክ አገልግሎት ለመስጠት በተደራጁ ቤተ-መፃህፍት  ወይም በህዝብ ቤተ-መፃህፍት ውስጥ የሚሰሩ የቤተ-መፃህፍት ባለሙያዎች በትልቁ ማህበር ሥር ራሳቸውን የቻሉ ክፍሎችን ወይም ቡድኖችን እንዲያቋቁሙ መርዳት ይገባል፡፡ እነዚህ ክፍሎች ወይም ቡድኖች በተደራጁባቸው ዝንባሌዎች ወይም የዕውቀት መስኮች በቦርዱ ወይም በአባላቱ ሊታይ ይገባል የሚሉትን ጉዳይ በማቅረብ፣ ወይም ከሌሎች ተመሳሳይ ዝንባሌ ካላቸው የውጪ ድርጅቶች ዘንድ ማህበሩን በመወከል በመገናኘት፣ እና ከእነሱ ጋር ተመሳሳይ ዝንባሌ ያላቸውና የማህበሩ አባል ያልሆኑ ሰዎች የማህበሩ አባል እንዲሆኑ በማግባባት ረገድ ጠቀሜታቸው ከፍ ያለ ነው፡፡

አብዛኛውን ጊዜ የወደፊት የማህበሩ መሪዎች የመጀመሪያ የመሪነት ልምዳቸውን የሚያገኙት ከእነዚህ የአካባቢያዊ ወይም ሙያዊ የዝንባሌ ቡድኖች ነው፡፡ ስለሆነም አሳታፊ የሆነ ድርጅታዊ አወቃቀር ጥቅሙ ተሳትፎን በማረጋገጥ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የማህበሩን አባላት የመሪነት ችሎታ በማዳበር በኩልም ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

### የሥራ ድርሻ ተጠሪነት አወቃቀር

አባላት ስለማህበራቸው የሥራ እንቅስቃሴ በቂ ዕውቀት እንዲኖራቸው ለማስቻል የሥራ ድርሻ ተጠሪነት አወቃቀር ማበጀት አስፈላጊ ነው፡፡ የሥራ ድርሻ ተጠሪነት አወቃቀር በማህበሩ ድርጅታዊ አወቃቀር ውስጥ መታየት ይኖርበታል፡፡ የማህበሩ አመራር አካል ከሁሉም የማህበሩ የሥራ ክፍሎች ማለትም ከኮሚቴዎች፣ ከክፍሎች፣ለአንድ ውሱን ለሆነ ተግባር የሚደራጁ

ግብረ-ሃይሎች እና ከመሳሰሉት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ የሥራ አፈፃጸም ሪፖርት ሊቀርብላቸው ይገባል፡፡ እነዚህ ሪፖርቶች  በማህበሩ የመረጃ ድር፣ዓመታዊ ሪፖርት ወይም በሌላ በማናቸውም ዓይነት መንገድ ለአባላቱ እንዲደርሱ ማድረግ ያስፈልጋል። አብዛኛውን ጊዜ የማህበሩ ከፍተኛ አመራር አካል በእነዚህ ሪፖርቶች አማካይነት በሚቀርቡ የውሳኔ ሃሳቦች ላይ ተወያይቶ ድምጽ ከሰጠባቸው በኋላ ውሳኔዎቹን ለአባላቱ ያስተላልፋል። በአንዳንድ ውሱን በሆኑና በማህበሩ ህገ-ደንብ ላይ በተመለከተው መሰረት በእነዚህ ከሥራ ክፍሎች በሚተላለፉ ሪፖርቶች ላይ መላው አባላት ድምጽ እንዲሰጡባቸው የሚጠየቅበት አጋጣሚ ይኖራል። እንዲሁም የማህበሩ ከፍተኛ አመራር አካል ለውይይት የቀረቡ ቃለ-ጉባዔዎችን ለአባላት እንዲደርሱ በማድረግ አመራሩ እየተወያየባቸው የሚገኙ ጠቃሚ ጉዳዮችን አባላቱ እንዲያውቋቸው ማድረግ ይኖርባቸዋል።